## መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

### አቅራቢዎች

# ኢየሱስ አስራ ሁለቱን ሐዋርያት መረጠ




ጸሐፊው: Edward Hughes
ምሣሌ አቅራቢው: Byron Unger; Lazarus
ያሻሸለው (አሻሸሎ የጻፈው): E. Frischbutter; Sarah S.
የተተረጎመው: Abel Eshetu
Alastair Paterson
አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org



BFC
PO Box 3
Winnipeg, MB R3C 2G1
Canada



©2020 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።




ኢየሱስ በርካታ ተዓምራትን አድርጓል።በሽተኞችን ፈውሷል፣ ለተቸገሩት ሰላምን ሰጥቷል፣የእግዚአብሔርንም ቃል አስተምሯል።




በርካታ ሰዎች ኢየሱስ እንዲፈውሳቸውና እንዲረዳችው ወደ እርሱ መጡ፤ ስለሆነም በዚህ አገልግሎት የሚረዱትን አስራ ሁለት ሐዋርያትን ለመምረጥ ወሰነ።
3


በጣም ወሳኝ የሆነ ጉዳይ ሲኖራችሁ ወደ እግዚአብሔር ትጸልያላችሁ? ኢየሱስ ግን ጸልዮ ነበር! ብቻውን በተራራ ላይ ይጸልይ ነበር። እስኪመሽ ድረስ ይጸልይ ነበር።
4


ሌሊቱን ሙሉ የጸለየበት ጊዜ ነበር።
5


ሲነጋም ኢየሱስ ተከታዮቹን ወደ እርሱ ጠራቸው። ከእነርሱም መካከል አብረውት እንዲያገለግሉ አስራ ሁለት ሐዋርያትን መረጠ።
6


መጀመሪያ የመረጣቸው ወንድማማቾቹን ስምዖን ጴጥሮስንና እንድርያስን ነበር።
7


ያዕቆብና ዮሐንስም የአሳ ማጥመጃ መረባቸውን ትተው ነበር የተከተሉት።
8

ፊልጶስ፣በርተለሜዎስ፣ማቴዎስ፣ቶማስ፣ቀናተኛው ስምዖን፣የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ፣ የያዕቆብ ወንድም ይሁዳ እንዲሁም ኢየሱስን የሸጠው የአስቆሮቱ ይሁዳ ከተመረጡት መካከል ይገኙበታል።



9

የእግዚአብሔርን ቃል መታተዝ ቤትን በአለት ላይ እንደመስራት ነው ብሎ ኢየሱስ አስተምሯል። ጽኑ ማዕበል ቢመታው ይህ አይነቱ ቤት አይፈርስም።



10

ቃሉን አለመታዘዝ ደግሞ ቤትን በአሸዋ ላይ እንደመስራት ሲሆን ማዕበል በመጣ ጊዜ ይህ ቤት ቶሎ ፈራሽ ይሆናል።



11

አንዳንዶቹ የኢየሱስ ትምህርቶች ቀላል አልነበሩም። “ቀኝህን ለሚመታህ ግራህን ስጥ”፤ “ጠላቶቻችሁን ውደዱ” ብሎ አስተምሯል። ኢየሱስ እንደሚለው ለመኖር የእግዚአብሔር እርዳታ ያስፈልጋል።



12

አንዳንድ ፈሪሳውያን ለታይታ እንደሚያደርጉት በአደባባይ ሳይሆን በስውር መጸለይ እንደሚገባ ኢየሱስ አስተምሯል።



13

እግዚአብሔር ለሚታመኑት ምግብንና ልብስን እንደሚሰጥ ኢየሱስ አስተምሯል። ልክ እግዚአብሔር ለወፎች ምግብን ለአበቦች ደግሞ የቀለማት ውበትን እንደሚሰጥ ሰዎች ለሚያስፈልጋቸው ነገሮች እርሱን መታመን ይኖርባቸዋል እያለ ኢየሱስ አስተምሯል።



14



በዚያ ቀን ኢየሱስ
ለአዳዲሶቹ ሐዋርያት በርካታ
ነገሮችአስተማራቸው።
ሲጨርስም አንድ ለምጻም
ሰው መጥቶ እንዲፈውሰው
ለመነው።

15



ኢየሱስም ለምጻሙን
በል እሺ ተፈወስ አለው።
ደቀመዛሙርቱም ሲመለከቱ
ለምጻሙ ተፈውሶ ነበር።
እነርሱም የሚከተሉት
ኢየሱስ ታላቅ እንደሆነ
ተረዱ።

16

ኢየሱስ አስራ ሁለቱን ሐዋርያት መረጠ

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 4-7
፤ የማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 1
፤የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 6

"የቃልህ ፍቺ ያበራል."
መዝሙረ ዳዊት 119:130

17

# መጨረሻ

39 60

18

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን
እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር "ኃጢአት" ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል።
የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን
አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት
እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው።
ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ!
ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል
ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤
እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት
ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ
ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን
ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና
እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16

19